# ባልደራስ ለእውነተኛ ዲሞክራሲ ፓርቲ የሶስት ዓመት የሰላማዊ ትግል ስልታዊ ዕቅዱን በብሄራዊ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ማስገምገሙን አስታወቀ፡፡

አማራ ሚዲያ ማዕከል/አሚማ
ህዳር 6 ቀን 2013 ዓ.ም
አዲስ አበባ ሸዋ

ትናንት ጥቅምት 5 ቀን 2013 ዓ.ም የባልደራስ ለእውነተኛ ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ የአደረጃጀት ጉዳይ ኃላፊ አቶ ጌታነህ ባልቻ እና የዝግጅት ቡድኑ አባላት አቶ እንድሪያስ በቀለና አቶ ገዛኸኝ ጌታሁን የፓርቲውን የሶስት ዓመት ስልታዊ የሰላማዊ ትግል ዕቅድን በዝርዝር ካቀረቡ በኃላ የስራ አስፈፃሚው ኮሚቴ ጥልቅ ውይይት ስለማድረጉ ፓርቲው በይፋዊ የማህበራዊ ትስስር ገጹ አስታውቋል።
በውይይቱ ላይ የተነሱ ፍሬ ሀሳቦችም በስልታዊ እቅዱ ላይ እንደሚካተቱ የዘርፉ ኃላፊ አስታውቀዋል፡፡
በባልደራስ ለእውነተኛ ዲሞክራሲ ፓርቲ በአባልነታቸው ምክንያት ለእስር የተዳረጉ ያላቸው አቶ ቢኒያም እና አቶ ከድር አሰፋ በውይይቱ ላይ ተካፋይ ነበሩ ብሏል፡፡
አቶ ከድር አሰፋ እና አቶ ቢኒያም በእስር ቤት የቆዩበትን ሁኔታ እና ያጋጠማቸውን ተግዳሮቶች ለስራ አስፈፃሚው ኮሚቴ ስለማብራራታቸው እንዲሁም የእስሩ ሂደት ፅናትን እንደሰጣቸው አስረድተዋል ተብሏል፡፡
የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴውም ታስረው ለነበሩ የፓርቲው አባላት የአድናቆት ሰርተፍኬት አበርክቶላቸዋል ሲል ባልደራስ በማህበራዊ ትስስር ገጹ አስፍሯል።